# በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን፡፡

## ስብከተ ወንጌል ትናንት፣ ዛሬና ነገ

# በኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

# ዓላማ

- በዚህ ርዕሰ ጉዳይ የተነሳበት ዓላማ ፡-
  - የቤተ ክርስቲያናችንን ነባራዊ የስብከተ ወንጌል እንቅስቃሴ መቃኘት
  - ዛሬ ካለው የስብከተ ወንጌል እንቅስቃሴ ጋር ማነጻጸርና
  - ወደፊት ሊተኮርባቸው የሚገቡ ጉዳዮችን መጠቆም ነው፡፡

# መግቢያ

- ቤተ ክርስቲያናችን ከጌታችን ከአምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተቀበለችውን የስብከተ ወንጌል አገልግሎት ስታከናውን የቆየች ሲሆን የስብከተ ወንጌል አገልግሎትዋ፣ አጠቃላይ ታሪክ፣ መንገዶችና ወርቃማ ዘመናት፣ የፈተና ወይም የድክመት ጊዜያት፣ ያጋጠሙ ችግሮች ውጤቶቻቸውን ስንመለከት የአሁኑ አገልግሎት መገለጫ የሆኑ ጠንካራና ደካማ ጎኖች የቀደመውን ተመርኩዘን ለመቃኘት እንሞክራለን፡፡
- የቀድሞ የስብከተ ወንጌል አገልግሎትን ስንቃኝ አራት ዋና ዋና ነጥቦችን እንመለከታለን፡፡

  1. የስብከተ ወንጌል መሠረት የተጣለባቸው ዘመናት
  2. ከመምህራን ወደ ምዕመናን - የወንበር ትምህርት
  3. ወርቃማ ዘመናት
  4. በስብከተ ወንጌል አገልግሎት የገጠሙ ፈተናዎች

# የስብከተ ወንጌል መሠረት የተጣለባቸው ዘመናት

- የሐዋርያት ስብከት
- የኢትዮጵያዊው ጃንደረባ መጠመቅ
- በንግድ፣ በስደት በተለያዩ ምክንያቶች ወደ አገራችን የገቡ ክርስቲያኖች

# ከመምህራን ወደ ምዕመናን - የወንበር ትምህርት

- አበው ሊቃውንት ትምህርት ቤት ከፍተው መጽሐፍ ዘርግተው ያስተማሩበት፣
- የዛሬው የትርጓሜና የጸሎት... መጻሕፍትን ያዘጋጁ መምህራን የወጡበት፣
- ሃይማኖት ከክህደትና ከኑፋቄ ተጠብቆ የጸናበት፣
- መደበኛ ትምህርት ቤቶች የተስፋፉበት ዘመን ሲሆን በዚህም ሂደት ብዙ ተተኪ መምህራን ተፈጥረዋል፡፡

# ወርቃማ ዘመናት

- ስብከተ ወንጌል ተጠናክሮ የተሰጠበት
- በሀገራችን ክርስትና እንደ ማንነት እስኪቆጠር የተስፋፋበት
- ሕንጻ አብያተ ክርስቲያናት መታነጽና ክርስትና ብሔራዊ ሃይማኖት መሆኑና መጽናቱ
- በዚህ ዘመን ተጠቃሽ ከሆኑ ሂደቶች መካከልም የሚከተሉት ሳይጠቀሱ የሚታለፉ አይደሉም፡፡

1. _አብርሃ ወአጽብሃ፦_ በአቡነ ሰላማ መሪነት በማኅበረ ጽዮን ና በሌሎችም አበው ጥረት ክርስትና ብሔራዊ ሃይማኖት ሆኖአል፡፡
2. _ተሰዓቱ ቅዱሳን፦_ በስብከታቸው ባደረሷቸውና ከአቡነ ሰላማ በተከተሉት መንገድ፣ ያላመኑትን አሳምነው ሲጠመቁ፣ አማንያን በምግባር ትሩፋትና ጸጋ እግዚአብሔር የበረቱበት አገልግሎት ነበር፡፡ በዚህም የተነሳ በአቡነ አረጋዊ ገዳም ብቻ ከ6000 በላይ መነኮሳት ዓለምን ንቀው የክርስቶስ ሙሽርነትን መርጠው መንኩሰዋል፡፡
3. _ከ12ኛው እስከ15ኛው መቶ ክ/ዘ፦_ በአራቱም አቅጣጫ በግልና በማኅበር ለሐዋርያዊ ተልዕኮ የተፋጠኑ አባቶች ብዙዎችን አጥምቀው ለሰማያዊ ሕይወት አብቅተዋል፡፡ ከነዚህም የምሁር ገዳም በአቡነ ማርቆስ መመሥረት፣ የአባ ጽጌ ድንግል ከይሁዲነት መመለስ፣ ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በደቡብ ያካሄዱት ስብከተ ወንጌልና ውጤቱ፣ የገዳማት መስፋፋትና መጠናከር፣ የመጻሕፍት በብዛት መተርጎምና የአብያተ ክርስቲያናት መታነጻቸው … የነገሥታቱ ብቸኛ ፍላጎት ፣ ከምድር የተገኘ ድንገተኛ አጋጣሚ ወይም ሌላ ሳይሆን የቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌል ድምር ውጤት ነበር፡፡

# የቀጠለ

በኅብረትና በማዕከላዊነት የተሰጡ አገልግሎቶች

- የደብረ በንኮሎ የአቡነ መድኃኒነ እግዚእ ገዳም ሰባቱ ከዋክብትና አምስቱ ቅዱሳን በስብከት፣ ትምህርት ቤትና ገዳም ለማስፋፋት የደከሙበት ዘመን ነበር፡፡
- ቤተ ኤዎስጣቴዎስ በአቡነ ኤዎስጣቴዎስ መሪነት ሕዝቡን በስብከት ፣ ገዳማትም በምንኩስና እንዲቀኑ አድርገዋል፡፡
- አቡነ ተክለሃይማኖት ራሳቸው ሰብከው ተማሪዎቻቸውንም አሰማርተው 33 ንቡራነ እድን በአገሪቱ ደቡብ፣ ምዕራብና ምሥራቅ ክርስትና እንዲስፋፋና አገር እንዲቃና አድርገዋል፡፡

# በስብከተ ወንጌል አገልግሎት የገጠሙ ፈተናዎች

1. *የውጪ ፡-* ዮዲት፣ ግራኝ፣ ካቶሊኮችና ፕሮቴስታንቶ፣ የእስልምና መስፋፋት... እነዚህ ሁነቶች የአብያተ ክርስቲያናትን መዘጋት፣ የስብከተ ወንጌል ማዕከላትን መዳከም፣ ለብዙ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትም በግፍ ማለቅ ምክንያት የሆኑ ሲሆኑ ተተኪ መምህራንንም አሳጥቷል፡፡ *ምሳሌ፡-* ከ13-15ኛ መቶ ክፍለ ዘመን በአራቱም አቅጣጫዎች የተስፋፋው ስብከተ ወንጌል ከ1527-1547 ዓ.ም. በተነሳው የግራኝ ወረራ ተጎትቶ ወደ ኋላ ተመልሷል፡፡
2. *የውስጥ፡-* ምንጩ የውጪ ፈተና ነው፡፡ በግራኝ ወረራ ወቅት የመጡት ካቶሊኮች ከብዙ ሺ ምዕመናን እልቂት በኋላም ቅባትና ጸጋ በሚሉ ክፍፍሎች ሊቃውንትን ለ300 ዘመናት ባልተቋጨ ሙግት ውስጥ እንዲገቡ ያደረገ ሲሆን የስብከተ ወንጌልም እንዳይስፋፋ ጎታች ሚና ተጫውቷል፡፡ በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን እውነተኞቹ ሐዋርያዊ ተልእኮውን ያስፋፉ ነበር፡፡

# የስብከተ ወንጌል አግለግሎት - ዛሬ

- ተጠያቂ መምህራን ያሉበት
- የዐውደ ምሕረት ጉባኤያትና የተስፋፉበትና የተዘረጉበት
- የመንፈሳዊ ኮሌጆች መከፈትና የሰንበት ት/ቤቶች መቋቋም የአገልግሎቱ ቅርጽ ሲያሰፋው መሠረታዊው የይዘት ጥንካሬው እንደነበረው  የቀጠለበት
- ከ1966 – 1980ዎቹ  ተዳክሞ የነበረው አገልግሎት እንደገና ማበቡ
- የቅዱስ ጳውሎስ፣የቅድስት ሥላሴና፣ የከሳቴ ብርሃን፣ ዝዋይ፣ አዋሳ፣ መቱ፣ አርባ ምንጭ፣ ባሕር ዳር፣ ሐይቅ እስጢፋኖስ…

ተቋማት መምህራንን በብዛት ማፍራታቸው፣ የመንፈሳዊ ማኅበራት የአገልግሎት አድማስ መስፋት

- የሠርክ ጉባኤያት በየአጥቢያው እንዲጠናከሩ፣ የሰንበት ት/ቤቶች እንዲጠናከሩና እንዲስፋፉ ማድረጉ
- የምዕመናን  ተምሮ እውነተኛውይቱን ኦርቶዶክሳዊ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናቸውን ለማወቅ የመፈለግ ፍላጎት መጨመር

# ችግሮቹ

- የመምህራን መኖር በገጠርና በከተማ ያልተመጣጠነ መሆን፡፡ በከተማ በአንድ ቦታ ብዙ ተጠያቂ መምህራን የሚገኙ ሲሆኑ በገጠር ለብዙ አብያተ ክርስቲያናት አንድም ለመገኘት አለመቻላቸው
- የመናፍቃን ሾልኮ መግባት ጠንካራ የስብከተ ወንጌልና የሰንበት ት/ቤት አገልግሎት የሚሰጡ ሰንበት ት/ቤቶችንና ጉባኤያትን በትኖአል፡፡ ለዚህም የሐረር መድኃኔዓለም፣ የናዝሬት ማርያም፣ የማህደረ ስብሐት ቅድስት ልደታ ለማርያም ፣ በፈረንሳይ አቦ አካባቢ የነበረው የመድኃኔዓለም ማኅበር ተጠቃሽ ናቸው፡፡
- በአፍ እንሰብካለን እያሉ በተግባር ቤተክርስቲያንን የሚያዳክሙ መናፍቃን ባያዳክሙአቸው ሰ/ት/ቤቶቹ ዛሬ የት በደረሱ ነበር፡፡
- ስብከቶቹ ምንጫቸው የመናፍቃን ቃላቸውና ቃላት አጠቃቀማቸው ኦርቶዶክሳዊ ይትበሃል የለቀቁ መሆናቸው
- የስብከት ምንጮቹ በግልጥ የመናፍቃን መጻሕፍት መሆኑም ሌላው ችግር ነው፡፡
- ሥጋዊ ዓላማና ምድራዊ ሐሳብን የተሞሉ፣ የሐሰት ባሕታውያን ስቶ ማሳት ከመናፍቃን ትችት ጋር ተዳምሮ በእንቅፋት ላይ ጆሮ ደግፍ መሆን
- ሌላው ሳይጠቀስ የማይታለፈው በቡድን በመሆን አንዱ የሌላውን ስም ማጥፋት፣ የቤተክርስቲያንን መዋቅራዊ አሠራር በሚዳፈር መልኩ የስብከተ ወንጌል ዐውደ ምሕረቶችንም ሆነ የምዕመናንን ሥነ ልቦና የሚጎዳ ከቤተ ክርስቲያን ዓላማ ውጪ የሆኑ አድራጎቶች መበራከት ነው

# ችግሮቹ ጠቅለል ባለ መልኩ

የስብከት ይዘትና አቀራረብ ችግሮች

1. መናፍቃዊ ይዘትና አቀራረብ
2. የእውቀት ማነስ
3. ሐሰተኛ ራዕይ ወይም ትንቢት

መሠረታዊ ችግሮች

1. የፓለቲካ መድረክ ማድረግ
2. የኑፋቄ ትምህርት ማስተላለፍ
3. ትክክለኛ የሆኑ የእውቀት ምንጮችን አለመጠቀም
4. ወደ አደባባይ ከመውጣት አስቀድሞ ወጥነት ያለው የደጅ ጥናት አቅጣጫዎች መዳከም

ተዛማጅ ችግሮች

1. መጠላለፍ
2. አለመደማመጥ
3. ወቅታዊ ችግሮች
4. የቤተ ክርስቲያን መዋቅሮችን ማዳከም
5. የሕይወት ምሳሌነት መዳከም - በወጣት አገልጋዮች
6. ውሎን መለየት አለመቻል፣ ንግግርንና ቦታዎችን አለመመጠን - መመጠን አለመቻል

# ለነገ ቢሆኑ ተብለው የሚጠቆሙ

- የቤተ ክርስቲያንን  የዕለት፣ የወራትና የዘመን  አካሄዶችን  በመከተል ወጥነት ያለው ትምህርት ከማዕከል እስከ አህጉረ ስብከቶች ፣ ወረዳዎችና፣ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት እንዲተገበር ቢደረግ
- በሰንበት ት/ቤትም የሚሰጡ ትምህርቶች ዕድሜን፣ የትምህርት ደረጃንና የኑሮ ሁኔታንም ባገናዘበ መልኩ በወጥነት እንዲሰጥ ቢደረግ
- በካሴት፣ በሲዲና በቪሲዲ የሚሰራጩ ትምህርቶችንና የዐውደ ምሕረት ትምህርቶችን ርቱዓዊነት የሚቆጣጠረው አካል ተጠናክሮ ውዥንብሮችና ግርግሮችንም መጠቂሚ የሚያደርጉትን ቢከላከል
- ማዕከላዊ አሠራሮች ቢጠናከሩ  በየመንደሩና በየሥርቻው በሚጸነሱ አሉታዊ ግርግሮች  በራስ የማስታገስ ዕድልን ሊፈጥር እንደሚችል ቢታሰብበት
- የሐዋርያዊ አገልግሎት ቋሚ መርሐ ግብር ቢኖርና ቢተገበር ምዕመናን ትምህርቱን ከምንጩ ለማግኘት ይችሉበታል፡፡ ለምሳሌ ወርሃዊ በወረዳ፣ ሩብ ዓመታዊ በሀገረ ስብከትና ኣመታዊ በአገር አቀፍ ደረጃ በጠቅላይ ቤተ ክህነት ቢካሄድ
- የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ፣ የሰ/ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ መመሪያዎች በበቂ የሰው ኃይልና በአቅም ቢጠናከሩ፣ ዘመናዊ ቴክኖሎጂን መጠቀም የበለጠ ቢጠናከር
- በጠቅላይ ቤተ ክህነት ሊሠራ የታሰበው የስብከተ ወንጌል ማዕከል ሥራ ቢፋጠን ሌሎችም በተጨማሪነት ቢታሰብባቸው
- የስብከተ ወንጌል አገልጋዮችን አቅም የሚያጠናክርና ማሰማራት የሚቻልበት ንድፍ ቢኖር

የቤተ ክርስቲያናችን አምላክ
አገልግሎትዋን ሁሉ የተሳካ
ያድርግልን - አሜን።